## Interest Free Banking (IFB) Diaspora Mortgage Financing

The commercial Bank of Ethiopia has designed Interest free mortgage financing for Ethiopians living abroad and foreigners of Ethiopian origin.

**Features of IFB Diaspora Mortgage Financing**

- **Purpose**: Purchase of residential houses.
- **Principle**: Based on Sharia'h through Murabaha financing.
- **Repayment schedule**: Maximum of twenty years.
- **Down payment**: At least 20% of the house to be purchased.
- **Profit Margin**: To be determined based on amount, life of financing and option of financing.

**How to open Wadia'h Diaspora Mortgage Savings (WDMS)**

- Applicants may approach branches of the bank with IFB windows service in person or through their agent to open Wadia'h based Diaspora Mortgage Savings account.
- Alternatively, applicants may consult Ethiopian Embassies to open the savings account.
- Applicants can lodge their financing request to IFB Financing Business in Addis Ababa or to District Offices out of Addis Ababa or the account opening branch, as appropriate and at their convenience.

**Who is Eligible to Wadia'h Dispora Mortgage Financing?**

- Ethiopian diaspora aged 18 years and above.
- Diaspora who can submit the following documents:
  - Residence and/or work permit, and renewed passport (for non-resident Ethiopians);
  - Renewed passport and "yellow card" (for non-resident foreigners of Ethiopian origin);
  - Two passport size photographs;
  - Marriage certificate, or otherwise;

    - If applicable, power of attorney, copy of ID and 2 passport size photographs of the agent (s);
    - Employment letter stating annual gross and net incomes from employer or individual tax return; (optional)
    - Copy of employment contract, if applicable;
    - Bank account statement of at least one year from a foreign bank;
    - If the applicant is a business person s/he shall present:
        - Financial statement for at least three consecutive years;
        - Renewed trade license and trade registration certificate; and
        - Tax payment certificate.
- The applicant shall pay at least 20% of the cost of the residential house to be purchased or constructed as down payment in foreign currency (USD, GBP, EURO).

# በውጭ ሀገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የቀረበ የቤት መግዣ የፋይናንስ አገልግሎት

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የቤት መሥሪያ ወይም መግዣ የፋይናንስ አገልግሎት አቅርቧል። ይህ አገልግሎት ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከወለድ ነፃ በሆነ አገልግሎት ባንኩ የሚሰጠውን የፋይናንስ አገልግሎት እንዲጠቀሙ የሚያስችል ነው።

## የቤት መግዣ ፋይናንስ አገልግሎት መገለጫዎች

- የፋይናንስ አገልግሎቱ ለመኖሪያ ቤት መግዣ ብቻ የሚውል ነው፤
- ባንኩ አገልግሎቱን የሚያቀርበው በሸሪያ መርህ የሙራባሃ አሰራርን ተከትሎ ይሆናል፤
- ደንበኛው የሽያጩን ክፍያ ለባንኩ ከፍሎ የሚያጠናቅቀው ከ20 ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ነው፤
- ደንበኛው የሚከፍለው ቅድመ-ክፍያ የሚገዛውን ቤት ዋጋ/ግምት ቢያንስ 20 በመቶ ይሆናል፤
- ባንኩ ላቀረበው የፋይናንስ አገልግሎት የሚያስከፍለውን የትርፍ መጠን በቤቱ ዋጋ፣ ክፍያ የማጠናቀቂያ ጊዜ ርዝማኔ፣ እና ደንበኛው በመረጠው የፋይናንስ አማራጭ የሚወሰን ይሆናል።

## የቤት መግዣ ቁጠባ ሂሳብ የት መክፈት ይቻላል?

- አመልካቹ ከ1,400 በላይ በሚሆኑት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወለድ አልባ የባንክ አገልግሎት የሚሰጡ ቅርንጫፎች ወይም በሚኖርበት ሀገር በሚገኝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ በአካል በመቅረብ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ አማካይነት የ”ወዲያ ቁጠባ ሂሳብ” በመክፈት ለመጀመሪያ ክፍያ የሚሆነውን ገንዘብ መቆጠብ ይችላል።
- አመልካቹ አዲስ አበባ ከሆነ የአገልግሎት ጥያቄውን ለባንኩ ወለድ አልባ የባንክ አገልግሎት ክፍል፤ ከአዲስ አበባ ውጭ ከሆነ ደግሞ ለሚመለከተው ዲስትሪክት ቢሮ ወይም የቁጠባ ሂሳቡን ለከፈተው ቅርንጫፍ ማቅረብ ይችላል።

## ለአገልግሎቱ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች

- ማንኛውም እድሜው 18 ዓመት እና ከዛ በላይ የሆነ ዳያስፖራ፣
- ዳያስፖራው አገልግሎቱን ሲጠይቅ የሚከተሉትን ሰነዶች ማሟላት ይኖርበታል፣

- አመልካቹ ኢትዮጵያዊ ከሆነ የታደሰ ፓስፖርት፣ የመኖሪያ እና/ወይም የሥራ ፈቃድ፤
- አመልካቹ ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ ዜጋ ከሆነ የታደሰ ፓስፖርትና የትውልደ ኢትዮጵያውያን መታወቂያ (ቢጫ ካርድ)፤
- ሁለት የቅርብ ጊዜ የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣
- የጋብቻ ምስክር ወረቀት፣ ወይም ያላገባ ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ሠነድ፣
- የአገልግሎቱ ጥያቄ የቀረበው በወኪል አማካይነት ከሆነ የተወካዩ የታደሰ መታወቂያ ኮፒ፣ሁለት ፓስፖርት መጠን ያላቸው የቅርብ ጊዜ ፎቶግራፎች እና የውክልና ማስረጃ፤
- እንደ አስፈላጊነቱ ጠቅላላ ዓመታዊ የደመወዝ መጠን እና የተጣራ ገቢን የሚገልጽ ከቀጣሪው የተሰጠ የቅጥር ደብዳቤ፣
- እንደ አግባብነቱ የቅጥር ውል ኮፒ፤
- ከውጪ ሀገር ባንክ ቢያንስ የአንድ ዓመት የሂሳብ መግለጫ፣
- አመልካቹ በንግድ ሥራ የሚተዳደር ከሆነ፣
  - የሦስት ተከታታይ ዓመታት የሂሳብ ዝርዝር መግለጫ፣
  - የታደሰ የንግድ ፈቃድ እና የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት (እንደአግባብነቱ)፣ እና
  - የግብር ክፍያ ምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርበታል።
- አመልካቹ የመኖሪያ ቤት መግዣውን ቢያንስ 20 ከመቶ በውጭ ምንዛሪ መክፈል አለበት፤
- የሽያጭ ሂደቱን ካጠናቀቀ በኋላ ደንበኛው የሚጠበቅበትን ወርሃዊ ክፍያ በባንኩ ተቀባይነት ባላቸው የውጭ ገንዘቦች (የአሜሪካን ዶላር፣ የእንግሊዝ ፓውንድ ወይም ዩሮ) መፈፀም አለበት።